# <u>የባሌ አማራዎች ወገኖቻችን ግድያ በአስቸኳይ ይቁም !</u>

<u>(ልሣነ ዐማራ- Amhara Press)</u>

በባሌ ጎባ ብዙ አማራዎች ለብዙ ዘመናት ተጋብተውና ተዋልደው ይኖራሉ፡፡ ከዚህ እውነታ በመውጣት በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ጽንፈኛ አማራ ጠል ብሔርተኞች በቀሰቀሱት ቅጭት አሁን በህይዎት የሌለዉ ጃራ አባ ገዳ የሚባል ሲመራው የነበረዉ የኦነግ ክንፍ አሁን ራሱን አደራጅቶ በአሁኑ ስዓት በባሌ ጎባ በሚኖሩ አማራዎች ላይ ከፍተኛ ጭፍጨፍ እየፈፀመ ይገኛል፡፡

ምንጮች እንደሚጠቁሙት የግጭቱ መነሻ “ቀይ ቀበሮ አደባባይ” የሚባለዉን አደባባይ “ሃጂ አደም ሳዶ” አደባባይ ብለን እንቀይረዋለን በሚሉ ከጎባ ከተማ ውጭ በመጡ ወጣቶችና በከተማው ሕዝብ መካከል የተፈጠረ አለመግባባት ነው።
ቦታው ታቦታት የሚያርፉበትና የሚያልፉበት መሆኑ እየታወቀ የሙስሊም አማኝ በሆኑ ግለሰቦች ስም እንዲሰየም ማድረግ ሆነ ተብሎ ሙስሊሙንና ክርስቲያኑን በማጋጨት ሰበብ ብሄርን ከብሄር ለማጋጨት የተጠነሰሰ እኩይ ሥራ እንደሆነና በቅርብ ሳምንታትም ይሄን ጉዳይ ለማስነሳት ሲሰሩ የነበሩ የደህንነት አካላትም እጃቸው እንዳለበት አረጋግጠናል፡፡

ትላንትና ዛሬም ለኦሮሞ ወጣቶች አንድ መኪና ሙሉ ገጀራና ሌሎች መሳሪያዎች ሲታደሉ የዋሉ ሲሆን ግጭቱ በኦሮሞ ሙስሊሞችና በአማራ ክርስቲያኖች መካከል የሃይማኖት ግጭት ሁኗል፡፡ በወቅቱም የጎባ አደባባይ ሲፈርስ የከተማው ፖሊስ ከኦሮሞ ወጣቶች ጋር ሁኖ ፎቶ ሲነሱ የነበሩ ሲሆን አማራዎችን ሲገድሉም እያዩ ምንም እርምጃ አለመዉሰዱ የፀጥታ አካላትም ተባባሪ መሆናቸዉን ያሳያል፡፡

የአካባቢው ህብረተሰብም ለአቶ ለማና ለአስተዳዳሪዎች ስልክ ደውለው ያናገሯቸው ሲሆን ምንም እርምጃ አልተወሰድም፡፡

ይህን ድርጊትም ለመከላከል በባሌ ጎባና አካባቢው የምትገኙ አማራዎች በአስቸኳይ በመደራጀትና በመነጋገር ራሳችሁን ታስተባብሩ ዘንድ የልሳነ-ዐማራ የዝግጅት ክፍል ጥሪውን ያስተላልፍል፡፡

ማስጠንቀቂያ

~~~~~~

1) የአማራ ክልል ብሔራዊ መንግስት እና

2) የኦሮሚያ ክልል ብሔራዊ መንግስት ባስቸኳይ በመነጋገር በብሔራቸውና በሃይማኖታቸው ምክንያት ጥቃት የሚደርስባቸውን አማራዎች ስቃይና ግድያ ማስቆም የማይቻል ከሆነ በኛ ቤት ያለው እሳትም መንደዱ አይቀርምና ባስቸኳይ ጥቃቱን እንድታስቆሙ እንጠይቃለን፡፡

ከዚህ በኋላ የሃገሪቱን ከፍተኛ የስልጣን ደረጃዎችና ሙሉ አሮሚያን አህዴድ በያዘበት ሰአት ህውሓትን ሽፍን በማድረግ በኦሮሚያ ክልል በሚኖሩ አማራዎች ላይ የሚደርሰውን ጥቃት ማስተባበል አይቻልም፡፡ ፀረ-አማራ የኦሮሞ አመራሮችና አክራሪ ብሔርተኞችም ከድርጊታቸው ይቆጠቡ ዘንድ እናስጠነቅቃለን፡፡
~~~~~~